አይርላድ

An Roinn Dlí agus Cirt,
Gnóthaí Baile agus Imirce
Department of Justice,
Home Affairs and Migration

euaa
EUROPEAN UNION
AGENCY FOR ASYLUM

# ለጥገኝነት ስለማመልከት ማወቅ ያለብዎት ነገር

## ያለ ወላጅ ለሚመጡ ሕፃናት መረጃ




ሰላም፣ እኛ ከተለያዩ አገሮች የመጣን ልጆች ነን። ጥገኝነት ለመጠየቅ ወደ አይርላድ ከመድረሳችን በፊት ረጅም መንገድ ተጉዘናል። ብቻችንን ያለ ወላጆቻችን ነው እዚህ የደረስነው።
ሰላም። ስሜ ሊሳ ይባላል። ስለ ጥገኝነት መጠየቅ (አለምአቀፍ ጥበቃ ተብሎም ይጠራል) ማወቅ ያለብዎትን ላስረዳዎ ነው።

# ዓለም አቀፍ ጥበቃ ምንድን ነው?







አንድ ሰው አደጋ ላይ ስለሚወድቅ ወደ አገሩ መመለስ ካልቻለ፣ ዓለም አቀፍ ጥበቃን ማግኘት እና ይህን ጥበቃ በሰጠው አገር ውስጥ በሰላም መቆየት ይችላል።

ማን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማግኘት እንደሚችል እና የአሠራር ሂደቱ ምን እንደሆነ ወኪሎች ተጨማሪ ያብራራል።

በአውሮፓ ውስጥ፣ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ጥገኝነት፣ የስደተኛነት ደረጃ ወይም አነስተኛ ጥበቃ ተብሎም ሊጠራ ይችላል። ምናልባት ጥገኝነት የሚለውን ቃል ሰምተው ይሆናል። ለማስታወስ ቀላል እንዲሆንልዎ ስለ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ስናገር ጥገኝነት የሚለውን ቃል እጠቀማለሁ።

# አሁን ደህንነትዎ የተጠበቀ እንደሆነ ያስታውሱ።


በአውሮፓ ውስጥ ሁሉም ሰው የመጡበት ቦታ፣ ሃይማኖታቸው ወይም የቆዳ ቀለማቸው ምንም ይሁን ምን በእኩልነት ይስተናገዳሉ።





በአውሮፓ ውስጥ፣ ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ሕፃን ተብሎ ይቆጠራል።

እንደ ሕፃን ደግሞ ልዩ መብቶች አሉዎት። የእርስዎ ደህንነት እና አጠቃላይ ጤንነት በጣም አስፈላጊ ናቸው።



እዚህ ላይ እንደሚታየው እንደ የጥገኝነት ባለሥልጣናት ሠራተኞች ያሉ የተለያዩ ባለሥልጣናትን ያገኛሉ። እነሱ ስለእርስዎ እና ወደ አውሮፓ ስለተጓዙበት ጉዞ ጥያቄዎችን ይጠይቁዎታል።

ባለሥልጣናቱ እዚህ ያሉት እርስዎን ለመጠበቅ እና ለእርስዎ የተሻለውን ለመወሰን እንደሆነ ያስታውሱ።

ምን እንደሚያስቡ፣ ምን እንደሚያስፈልግዎ እና ምን እንደሚሰማዎት ሁል ጊዜ ለባለሥልጣናቱ ማካፈል ይችላሉ።



# ወኪሎች ማን/ምንድ ነው?





ያለ ወላጆችዎ እዚህ ስለመጡ፣ ባለሥልጣናቱ የሚደግፍዎትንወኪሎች የሚባል አዋቂ ሰው ይመድባሉ።

አሳዳጊ ወላጆቻቸው ወይም ሌላ ኃላፊነት ያለባቸው አዋቂ ሳይዙ ወደ አውሮፓ የሚመጡ ሕፃናትን የሚረዳ ሰው ነው።

አሳዳጊ ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል።
ወኪሎችወኪሎችዎ ተብለውም ሊጠሩ ይችላሉ።

ወኪሎች ጋር ገና ካልተገናኙ፣ በተቻለ ፍጥነት ያገኙታል።

አንዳንድ ጊዜ፣ ቋሚ ወኪሎችን እስኪያገኙ ድረስ ባለሥልጣናቱ እርስዎን ለመደገፍ መጀመሪያ ጊዜያዊወኪሎች ሊመድቡ ይችላሉ።





አሳዳጊ እዚህ ያለው ስለ ቆይታዎ ማወቅ ያለብዎትን ሁሉ ለማስረዳት እና አስፈላጊ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ ለመርዳት ነው። ለምሳሌ፣ወኪሎች በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ ይረዱዎታል፣ የአሠራር ሂደቶችን ያብራራሉ፣ መብቶችዎን እና ግዴታዎችዎን ያብራራሉ፣ እንዲሁም ከባለሥልጣናት ጋር በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ከእርስዎ ጋር ይሳተፋሉ።

ለአሳዳጊው ሁል ጊዜ አስተያየትዎን መናገር፣ ጥያቄዎችን መጠየቅ እና የሚያስፈልግዎትን ነገር መንገር ይችላሉ። እዚህ ያሉት እርስዎን ለመደገፍ ነው።



ከወኪሎች ጋር ችግር ካለብዎት፣ ለባለሥልጣናቱ ይንገሩ። ይህ በጥገኝነት ማመልከቻዎ ላይ በአሉታዊ መልኩ ተጽዕኖ አይኖረውም።



# በሂደቱ ወቅት ምን አይነት እርዳታ ይሰጣል?





ደህንነቱ የተጠበቀ የመቆያ ቦታ



ልብሶች



ሊያስፈልጉዎት የሚችሉ ሌሎች ነገሮች



ምግብ



ወደ ዶክተር መሄድ ይችላሉ



ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ



ለእርስዎ ጥሩ በሆነ ቦታ ይኖራሉ እና እንደ እድሜዎ የሚፈልጉትን እርዳታ ያገኛሉ።

# ጥገኝነት ጠየቅኩኝ፣ ቀጥሎ ምን ይሆናል?






**በመጀመሪያ ማመልከቻዎ መመዝገብ እና መቅረብ አለበት።**

የጥገኝነት ጥያቄ ባቀረቡ በ 10 ቀናት ውስጥ ማመልከቻዎ ይመዘገባል እንዲሁም በዚያው ቀን ይገባል።

ከዚያም ከተመዘገቡ በኋላ በ 21 ቀናት ውስጥ ማመልከቻዎን ማቅረብ አለብዎት።

የእርስዎወኪሎች የእርስዎ ጊዜያዊወኪሎች በሚኖሩበት ቦታ የሚሰሩ አዋቂዎች ስለ  ቀኑ ቀናት እና ሰዓቱ ሰዓቶች ያሳውቁዎታል፣ እንዲሁም ወደ ባለሥልጣናት ሲሄዱ የእርስዎወኪሎች ያጅብዎታል።

ወኪሎች በሂደቱ ወቅት ከእርስዎ ጋር ይሆናል።



## በማመልከቻ ምዝገባ እና ማቅረብ ወቅት የሚከተለው ይሆናል...





እጅዎ ላይ የሚገኙት ማንኛውንም የመለያ ሰነዶች (ፓስፖርት፣ መታወቂያ ካርድ፣ ወዘተ) ለባለሥልጣናት ያሳያሉ።

እርስዎ እና የግል ንብረቶችዎ መፈተሽ ይቻል ይሆናል። ባለሥልጣናቱ ንብረቶችዎን ለተወሰነ ጊዜ ሊይዙ ይችላሉ፣ ነገር ግን አደገኛ ከሆኑትን ንብረቶች በስተቀር ሁሉንም ነገር ይመልሱልዎታል።





ፎቶግራፍ ይነሳሉ።

የጣት አሻራዎችዎ ይወሰዳል።







ዶክተር ሊያዩ ይችላሉ

- አንድ ባለሥልጣን ስለእርስዎ እና በአውሮፓ ስለሚገኘው ቤተሰብዎ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል

አንድ ባለሥልጣን የእውቂያ መረጃዎን (አድራሻዎ እና ስልክ ቁጥርዎን) እንዲሰጡ ይጠይቅዎታል።



ስለሚከተለው ተጨማሪ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ፡-

- ስለ እርስዎ እና ቤተሰብዎ
- ስለ ሀገርዎ እና ከዚህ በፊት ስለኖሩባቸው ቦታዎች
- ሀገርዎን ለምን ለቀው እንደወጡ እና ለምን መመለስ እንደማይፈልጉ
- ወደ አይርላድ እንዴት እንደተጓዙ



## ያስታውሱ!

ከወኪሎች ጋር መነጋገር እና ከጥገኝነት ባለሥልጣናት ጋር አብሮ መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው።



ለወኪሎች ወይም ለባለሥልጣናቱ የሚናገሩት ነገር **ሚስጥራዊ ሆኖ ይቆያል**። ይህ ማለት የሚሰጡት መረጃ ለእርስዎ ሀገር መንግሥት ወይም ለሚፈሯቸው ሰዎች ፈጽሞ አይተላለፍም ማለት ነው።




# በጥገኝነት ሂደት ውስጥ በ አይርላድ እቆያለሁ?





ከምዝገባ በኋላ፣ ባለሥልጣናቱ ማመልከቻዎን የሚመረምረው የትኛው ሀገር እንደሆነ ይወስናሉ። ወይ አይርላድ ወይም ሌላ የአውሮፓ አገር ይሆናል። አገሪቱን መምረጥ አይችሉም፣ ነገር ግን የእርስዎ ከፍተኛ ጥቅም ግምት ውስጥ ይገባል። ባለሥልጣናቱ ይህን ያብራሩልዎታል።





በምዝገባ ወቅት ለባለሥልጣናት የሚከተለውን መንገርዎ አስፈላጊ ነው፡-

- በሌላ የአውሮፓ አገር ቤተሰብ ካለዎት
- ከዚህ በፊት በሌላ የአውሮፓ አገር ጥገኝነት ጠይቀው እንደሆነ።

በአውሮፓ ውስጥ ቤተሰብ ካለዎት፣ ስለ ቤተሰብዎ የሚያውቁትን ሁሉ ለባለሥልጣናት መንገር አስፈላጊ ነው። በዚህ አገር ወይም እነሱ በሚኖሩበት አገር ከእነሱ ጋር መቆየት ይቻል ይሆናል።

ቤተሰብዎ የት እንዳለ ካላወቁ፣ ወይም ግንኙነት ካቋረጡ፣ ቤተሰብዎን ለማግኘት የእርዳታ ጥያቄ፣ ለወኪሎችን መጠየቅ ይችላሉ።



# ከማመልከቻ ምዝገባ እና ማቅረብ በኋላ ምን ይሆናል?





ከምዝገባ በኋላ፣ ማመልከቻዎ መደረጉን እና መመዝገቡን የሚገልጽ (ጊዚያዊ) ሰነድ ይደርስዎታል።

ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ ጥገኝነት እንደጠየቁ የሚገልጽ ሰነድ ይሰጥዎታል። ይህ ሰነድ አስፈላጊ ነው፣ ስለዚህ በጥንቃቄ ይያዙት። ከሚኖሩበት ቦታ ሲወጡ ወይም ከባለሥልጣናት ጋር ስብሰባ ሲኖርዎት ሁል ጊዜ ይዘውት ይሂዱ።



# ባለሥልጣናቱ ዕድሜዬን እንዴት ያውቃሉ?





ዕድሜዎን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ከሌሉዎት እና ባለሥልጣናቱ ስለ ዕድሜዎ ጥርጣሬ ካደረባቸው፣ የጥገኝነት ባለሥልጣናት ሠራተኞች የዕድሜ ግምገማ ውስጥ እንድያልፉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ይህ እድሜዎን ለመገመት የሚረዳ ሂደት ነው።

ዕድሜዎን ለመገመት የተለያዩ መንገዶች አሉ።

ለምሳሌ፣ ባቀረቧቸው ሰነዶች ወይም ከባለሥልጣናት ወይም ከተለያዩ ስፔሻሊስቶች ጋር ባደረጉት ቃለ-መጠይቆች ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። ተጨማሪ ጥርጣሬዎች ካሉ፣ የህክምና ምርመራ እንዲያደርጉ ሊጠየቁ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ፣ እርስዎ እና ወኪሎች ፈቃድ እንድትሰጡ ትጠየቃላቹ።

የዕድሜ ግምገማው ከ18 ዓመት በላይ እንደሆኑ ከወሰነ፣ አዋቂ ተብለው ይቆጠራሉ። በዚህ ሁኔታ፣ ተጨማሪ መረጃ ይቀበላሉ።





ባለሥልጣናቱ አንድ ሰው እንደጎዳዎት ከተሰማቸው፣ ዶክተር እንዲያዩ ያቀርቡልዎታል።

የህክምና ምርመራው ውጤት ማመልከቻዎን በሚመረምሩበት ጊዜ ግምት ውስጥ ይገባል።



**ማመልከቻዎ ከቀረበ በኋላ፣ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የግል ቃለ-መጠይቆች ሊኖሩዎት ይችላሉ።**

ይህ ማለት አንድ ባለሥልጣን ስለእርስዎ፣ አገርዎን ለምን እንደለቀቁ እና መመለስ የማይፈልጉት ለምንድን ነው በሚለው ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል ማለት ነው። ባለሥልጣናቱ በቃለ-መጠይቅ ውስጥ እንድትሳተፉ ከጠየቁዎት፣ መገኘት እና ሊያስታውሱት የሚችሉትን ሁሉ መናገር አለብዎት። የግል ቃለ መጠይቁ በድምጽ ይቀዳል።

ወኪሎች ቃለ-መጠይቁ መቼ እና የት እንደሚካሄድ ይነግርዎታል እና በቃለ-መጠይቁ ወቅትም ይደግፍዎታል።



# ባለሥልጣናቱ የሚያወሩትን ቋንቋ ካልገባኝስ?





የባለሥልጣናቱን ቋንቋካልተረዱ፣ ቋንቋዎን የሚናገር ተርጓሚ እንዲረዱዎት ይረዳዎታል።

ተርጓሚ የሚነገረውን ከመተርጎም ውጪ በጉዳይዎ ውስጥ ሌላ ሚና የለውም። ለጉዳዩ ኃላፊ እና ለተርጓሚው የሚናገሩት ነገር ሚስጥራዊ ሆኖ ይቆያል።

በበለጠ ምቾት የሚሰማዎትን መሰረት በማድረግ፣ ቃለ-መጠይቅ አድራጊዎ ወይም ተርጓሚዎ ሴት ወይም ወንድ እንዲሆን መጠየቅ ይችላሉ። ምርጫዎ የሚቀርበው የሚገኝ ከሆነ ነው። ሴት ወይም ወንድ ምርጫ ካለዎት በተቻለ ፍጥነት እና ከቃለ-መጠይቁ በፊት ለወኪሎች ይንገሩ።



# ይህ ሁሉ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?







ከቃለ-መጠይቁ በኋላ የሰጡት መረጃ ሁሉ ይመረመራል።

ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ውሳኔዎን ለመቀበል እስከ **6 ወራት** ድረስ መጠበቅ ሊያስፈልግዎ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ፣ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፣ ነገር ግን **ከ21 ወራት** በላይ ሊወስድ አይገባም። መጠበቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ታጋሽ ይሁኑ። ባለሥልጣናቱ ለእርስዎ ትክክለኛውን ውሳኔ መስጠት ይፈልጋሉ።

የጥበቃ ጊዜውን ለመቋቋም እርዳታ ከፈለጉ ሁል ጊዜ ወኪሎችን መጠየቅ ይችላሉ።



## አንድ ጓደኛዬ ባለሥልጣናት የጥገኝነት ማመልከቻውን እንደማይገመግሙት ነግሮኛል። ይህ ለምን ሆነ?





ባለሥልጣናቱ በመጀመሪያ የጥገኝነት ማመልከቻ መመርመር ያስፈልጋቸው እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ያጣራሉ።

በሌላ አገር ውስጥ ጥበቃ ቀደም ብለው ከተሰጠዎት ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ብለው ከሚያምኑበት አገር ከመጡ ባለሥልጣናቱ ማመልከቻዎን ሙሉ በሙሉ ላይመረምሩ ይችላሉ።

# ምን ዓይነት ውሳኔ እቀበላለሁ?





የጥገኝነት ባለሥልጣናት ጥገኝነት እንደሚያስፈልግዎት ወይም ለእርስዎ ሌሎች አማራጮች እንዳሉ ይወስናሉ።

ውሳኔው ለእርስዎ ይብራራልዎታል።



አሉታዊ ውሳኔ ከተቀበሉ እና እርስዎ ወይም ወኪሎች ካልተስማሙ፣ ውሳኔውን ወደ ፍርድ ቤት ወስደው መቃወም ይችላሉ። ይህ ይግባኝ (Appeal) ይባላል።






# ስለ ጥገኝነት ሂደቱ ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?





ከወኪሎች በተጨማሪ፣ ስለ ጥገኝነት ሂደት፣ ስለ መብቶችዎ እና ስለ ግዴታዎችዎ ሊያስረዱዎት የሚችሉ የህግ አማካሪዎች አሉ።

እነሱን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ወኪሎችን ይጠይቁ።



ጠበቃ እንዲረዳዎ ከፈለጉ፣ ከወኪሎች ወይም ከሌላ ባለሥልጣን ጋር ይነጋገሩ።





## ጠበቃው ከወኪሎች ጋር በመሆን በሚከተሉት ሊረዱዎት ይችላሉ፡-



ከባለሥልጣናት ጋር ለሚደረገው ቃለ-መጠይቅ መዘጋጀት።



ከጥገኝነት ባለሥልጣናት ጋር መነጋገር።



ስለ ጥገኝነት ማመልከቻዎ የተሰጠውን ውሳኔ መረዳት እና እርስዎ ወይም ወኪሎች ከውሳኔው ጋር ካልተስማሙ ይግባኝ ማለት።



በጥገኝነት ሂደትዎ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ UNHCRን ማነጋገር ይችላሉ።

UNHCR ጥገኝነት ፈላጊዎችን እና ስደተኞችን ይደግፋል እና ጥበቃ ያደርጋል።

ለUNHCR የሚሰሩ ሰዎች ለጥገኝነት ጠያቂዎች መረጃ እና እርዳታ ይሰጣሉ። ተጨማሪ መረጃ በ https://help.unhcr.org/ ማግኘት ይችላሉ።



UNHCR
The UN Refugee Agency



# ደህና ካልሆንኩ ወይም ብዙ ጊዜ የምጨነቅ ከሆነ እርዳታ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?



የሚከተሉት ነገሮች ከተከሰቱ ለወኪሎች፣ ለባለሥልጣን ወይም በሚኖሩበት ቦታ ለሚሰሩ ሰራተኞች ይንገሩ፡-




አንድ ሰው ቢጎዳዎት


ሐዘን፣ ቁጣ፣ ፍርሃት ከተሰማዎት ወይም ለመተኛት ከከበደዎት

ሌላ እንደ አካል ጉዳተኝነት ወይም ህመም ያለ ማንኛውም ችግር ካለብዎት ወይም ነፍሰ ጡር ከሆኑ

በእንደዚህ ዓይነትሁኔታዎች ውስጥ እርዳታ ያገኛሉ

# የሆኑ አይነት ግዴታዎች አሉብኝ?





**አዎ!**

**የዚህን አገር ህጎች እና ደንቦች መከተል አለብዎት።**

ስለ ደንቦቹ ወይም ህጎች ጥርጣሬ ካለዎት ወኪሎችን ይጠይቁ።




**ወኪሎች እንድትቆዩበት በነገራችሁ ቦታ መቆየት አለብዎት።**

ባለሥልጣናቱ ለእርስዎ የሚሆን ቦታ ይመርጣሉ። ከባለሥልጣናት ፈቃድ ውጭ አይሸሹ ወይም አይርላድን አይልቀቁ።



**ከባለሥልጣናቱ ጋር አብረው መሥራት አለብዎት።**

ሲጠየቁ፣ ለጥያቄዎቻቸው መልስ መስጠት እና መመሪያዎቻቸውን መከተል አለብዎት።



**እውነተኛ ይሁኑ እና ባለሥልጣናቱ ጥያቄ ሲጠይቁዎት የሚያውቁትን ሁሉ ይንገሩ።**

የሚናገሩት ነገር ለማመልከቻዎ በጣም አስፈላጊ ነው።

ሁሉንም ነገር ላያስታውሱ ስለሚችሉ፣ ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስ ላይችሉ ይችላሉ። ማስታወስ ካልቻሉ፣ መልስ አይፍጠሩ፣ ማስታወስ እንዳልቻሉ ብቻ ያስረዱ።

**ከባለሥልጣናት ጋር በሚደረጉ ሁሉም ቀጠሮዎች ላይ መገኘት አለብዎት።**

እነዚህ ቀጠሮዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው።
በተሰጠዎት ቀን እና ሰዓት መቅረብ አለብዎት።







**ትክክለኛ የእውቂያ ዝርዝሮችን መስጠት አለብዎት።**

ሁሉንም መረጃዎች እና ቀጠሮዎች ማግኘትዎን ለማረጋገጥ፣ለባለሥልጣ ናት አድራሻ ወይም ስልክ ቁጥር መስጠት አለብዎትወኪሎችው ይህንን መረጃም ይቀበላል እና ቀጠሮዎችዎን ሊያስታውስዎት ይችላል። የእውቂያ ዝርዝሮችዎ ከተቀየሩ፣ ለወኪሎች እና ለጥገኝነት ባለሥልጣናት ሠራተኞች ይንገሩ። እነሱ ሊያገኙዎት መቻል አስፈላጊ ነው።

**ያሉዎትን ሁሉንም ሰነዶች ለባለሥልጣናት መስጠት አለብዎት።**

ከእርስዎ ጋር የሚዛመዱ እና አገርዎን የለቀቁባቸውን ምክንያቶች የሚያሳዩ ያሉዎትን ሁሉንም ሰነዶች ይስጧቸው። ይህ የመታወቂያ ሰነዶችን (ፓስፖርት)፣ የልደት ወይም የትምህርት ቤት የምስክር ወረቀት፣ የህክምና ሰነድ ወይም ሌሎች ሰነዶችን ያጠቃልላል።

ሁሉንም መረጃ እና ሰነዶች በተቻለ ፍጥነት ማቅረብ አለብዎት።

አሁን ሰነዶቹ ከሌሉዎት፣ በኋላ ላይ ማቅረብ ይችላሉ። ከወኪሎች ጋር ይነጋገሩ። ወኪሎች እነዚያን ሰነዶች እንዲያገኙ እና በወቅቱ ከባለሥልጣናት ጋር እንዲያጋሯቸው ሊረዳዎ ይችላል።

**ግዴታዎችዎን መወጣት ካልቻሉ፣ ወዲያውኑ ለወኪሎች እና ለጥገኝነት ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ይንገሩ እና ምክንያትዎን ያስረዱ።**





# ግዴታዎቼን ካልተወጣሁ ምን ይሆናል?



ግዴታዎችዎን ካልተወጡ፣ በማመልከቻዎ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

ያብራራኋቸውን አንዳንድ መብቶች እና የድጋፍ አገልግሎቶች ሊያጡ ይችላሉ።



**ግዴታዎችዎን ካልተወጡ፣ የጥገኝነት ሂደትዎ ሊቆም ወይም ሊከለከል ይችላል፣ ለምሳሌ፦**

- ከባለሥልጣናት ለሚቀርቡት ጥያቄዎች መልስ ካልሰጡ፣ ወይም
- የጣት አሻራዎን እንዲወስዱ ካልፈቀዱ፣ ወይም
- ያለፈቃድ የሚቆዩበት ቦታን ከለቀቁ።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች፣ ባለሥልጣናቱ ማመልከቻዎ በቁም ነገር እንዳልወሰዱት ያስባሉ። አመልካች መሆንዎን ያቆማሉ እና የሚሰጠውን ሁሉንም ድጋፍ ያጣሉ።





ስለራስዎ ወይም ስለ ታሪክዎ እውነት የሆነውን ለባለሥልጣናት ካልነገሩ ወይም አስፈላጊ መረጃ ከደበቁ ወይም ሆን ብለው ሰነዶችዎን ካጠፉ፣ ማመልከቻዎ ሊከለከል እና ጥገኝነት ላይሰጥዎ ይችላል።


ባለሥልጣናቱ በኋላ ላይ በጥገኝነት ሂደት ውስጥ እውነቱን እንዳልተናገሩ ካወቁ፣ የተሰጦት ጥበቃ ከእርስዎ ሊወሰድ ይችላል።






ማወቅ ያለብዎትን በጣም አስፈላጊ ነገሮችን አስረድቻለሁ። ወኪሎች እና ባለሥልጣናቱ በጥገኝነት ሂደት ውስጥ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ይሰጡዎታል።




ያስታውሱ!
ጥገኝነት መጠየቅ ከክፍያ ነፃ ነው






# ጥንቃቄ ያድርጉ

በገንዘብ ወይም ውለታ ተቀብለው እርዳታ ከሚሰጡ ሰዎች ይጠንቀቁ። መጥፎ ዓላማ ሊኖራቸው ይችላል።



አንድ ሰው እንዲለቁ ሊያበረታታዎት ይችላል። ነገር ግን መውጣት እንደሌለብዎት ያስታውሱ፣ ምክንያቱም ይህ ለእርስዎ አደገኛ ሊሆን ይችላል እና።






የማይፈልጉትን ወይም ስህተት የሚመስለውን ነገር እንዲያደርጉ አንድ ሰው ሊያሳምኖዎት ከሞከረ ወዲያውኑ ለወኪሎች ወይም በሚቆዩበት ቦታ ለሚሠሩ አዋቂዎች ይንገሩ።



## ወደ ሀገሬ መመለስ እና ማመልከቻዬን ማቆም ከፈለግኩ ምን ማድረግ አለብኝ?





ወደ ሀገርዎ መመለስ እና ማመልከቻዎን ማቆም ከፈለጉ፣ ለወኪሎች እና ለባለሥልጣናት ይንገሩ። በደህና እንዲመለሱ ሊረዱዎት ይችላሉ።



# አሁን ስላስረዳሁዎት ነገር ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወኪሎችን፣ ባለሥልጣናቱን ወይም በሚቆዩበት ቦታ የሚሠሩትን ሠራተኞች ይጠይቁ።



ይህ ብሮሸር ለመረጃ አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም። የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት ኤጀንሲ (EUAA) የዚህን ጽሑፍ ዋና ክፍል አቅርቧል፣ እና የዚህ መግለጫ ቅጂ ማውጣትና ማሻሻያ ማድረግ የተፈቀደውለኢ.ዩ. አባል ሀገራት ብቻ ነው። EUAA በዚህ ገጽ ውስጥ በባለስልጣናት ወይም በማንኛውም ኃላፊነት የሚሰማው ሶስተኛ አካል ለተካተቱት መረጃዎች ትክክለኛነት፣ ይዘት፣ ምሉእነት፣ ህጋዊነት ወይም አስተማማኝነት ማንኛውንም ሃላፊነት አይወስድም ወይም ተጠያቂነት የለበትም፡፡ በዚህ ብሮሸር ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም EUAA ሆነ ማናቸውም በEUAA ስም የሚሰራ ማናቸውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025